23- ናዝሬት ወደምትባል ከተማም ሄዶ መኖር ጀመረ። በዚህም በነቢያት፣ «ናዝራዊ ይባላል» ተብሎ የተነገረው ትንቢት ተፈጸመ።

- ዮሴፍ ማርያምና ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።

- ዮሴፍ ኢየሱስንና ማርያምን ወደየትኛው ከተማ ወሰዳቸው?

- ወደ ናዝሬት ከተማ።

- እግዚአብሔር ከዘመናት በፊት በነቢያት አማካይነት በተናገረው መሰረት ኢየሱስ በናዝሬት ከተማ ኖረ።

- እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ፈጽሞ አያፈርስም።

- እግዚአብሔር ሁልጊዜም ተስፋዎቹን ይፈጽማል።



## ትምህርት 46

1. ኢየሱስ የመጣው ከማን የዘር ሐርግ ነበር?

ሀ- ከአብርሃም ከይስሐቅና ከያዕቆብ የዘር ሐረግ።

2. ኢየሱስ የመጣው ከየትኛው የአይሁድ ንጉሥ የዘር ሐረግ ነበር?

ሀ- ከንጉሥ ዳዊት የዘር ሐረግ።

3. «ክርስቶስ» የሚለው የኢየሱስ ስም ትርጉም ምንድን ነው?

ሀ- «ክርስቶስ» ማለት ነቢይ፥ ካህንና ንጉስ ማለት ነው።

4. ማርያም በማርገዟ ዮሴፍ ምን አሰበ?

ሀ- ዮሴፍ ማርያም ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደ ፈጸመች አሰበ።

5. ማርያም ከወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽማለች?

ሀ- አልፈጸመችም።

6. ታዲያ ማርያም እንዴት ልታረግዝ ቻለች?

ሀ- እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተአምር ስለሰራ ማርያም አረገዘች።

7. መልአኩ ዮሴፍን በሕልም ምን አለው?

ሀ- መልአኩ፥ ማርያም የጸነሰችው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተአምር በመሥራቱ መሆኑን ተናገረ።

8. «አማኑኤል» የሚለው ስም ትርጉም ምንድን ነው?

ሀ- አማኑኤል ማለት «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር» ማለት ነው።

9. ኢየሱስ አማኑኤል ተብሎ የተጠራው ለምን ነበር?

ሀ- ምክንያቱም ኢየሱስ ከሰዎች ጋር ሊኖር የመጣ አዳኙ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

- ማርያም የመውለጃዋ ጊዜ በደረሰ ጊዜ ወንድ ልጅ ወለደች።

- ማርያም ወንድ ልጅ ወለደች ሌላ ስፍራ ስለሌለ በጨርቅ ጠቅልላ በከብቶች መመገቢያ ግርግም ውስጥ አስተኛችው።

- ማርያምና ዮሴፍ የሕፃኑን ስም ኢየሱስ አሉት።

- ኢየሱስ አዳኙ እግዚአብሔር ቢሆንም እንኳ በተወለደበት ጊዜ የተኛው በከብቶች መመገቢያ ግርግም ውስጥ ነበር።

- ኢየሱስ የተወለደው በየትኛው አገር ነበር?

- በእስራኤል አገር።

- ኢየሱስ የተወለደው በየትኛው ከተማ ነበር?

- በቤተልሔም ከተማ።

- ኢየሱስ እኛን ከኃጢአት ኃይል ለማዳን ተወለደ።

- ኢየሱስ እኛን ከሞት ኃይል ለማዳን ተወለደ።

- ኢየሱስ እኛን ከሰይጣን ኃይል ለማዳን ተወለደ።



- ንጉሥ ሄሮድስ ከሞተ በኋላ በድጋሚ ዮሴፍን እንዲያናግር እግዚአብሔር መልአኩን ላከ፡

ማቴዎስ 2፡19 - 20

19- ሄሮድስ ከሞተ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ተገልጦ፣

20- «ተነሣ፣ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ እስራኤል ምድር ተመለስ፤ ሕፃኑን ለመግደል የሚሹት ሞተዋልና» አለው።

- መልአኩ ዮሴፍን ምን አለው?

- መልአኩ ዮሴፍን ንጉሥ ሄሮድስ ሞቶአል አለው።

- መልአኩ ዮሴፍን ማርያምንና ሕፃኑን ይዞ ወደ እስራኤል አገር እንዲመለስ ነገረው።

- ዮሴፍ መልአኩ የነገረውን በመታዘዝ ማርያምንና ኢየሱስን ይዞ ወደ እስራኤል አገር ተመለሰ።

ማቴዎስ 2፡21-23

21- ዮሴፍም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን በመያዝ ወደ እስራኤል ምድር ተመለሰ፤

22- ነገር ግን አርኬላዎስ በአባቱ በሄሮድስ ቦታ በይሁዳ መንገሡን በሰማ ጊዜ ወደዚያ መሄድ ፈራ። ጌታ በሕልም ስላስጠነቀቀው፣ ወደ ገሊላ አውራጃ ሄደ።

- ሰይጣን አዳኙ እንደሚመጣና እንድሚያሸንፈው አውቋል።

- ስለዚህም ሰይጣን ኢየሱስን ሊገድለው ሞከረ።

- ሰይጣን ሄሮድስ ኢየሱስን እንዲገድል ነገረው።

- እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን ጠብቆታል?

- አዎን።

- እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን የጠበቀው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር አብ ኢየሱስ ሰዎችን ከኃጢአት ኃይል እንዲያድናቸው ስለ ላከው ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር አብ ኢየሱስ ሰዎችን ከሞት ኃይል እንዲያድናቸው ስለ ላከው ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር አብ ኢየሱስ ሰዎችን ከሰይጣን ኃይል እንዲያድናቸው ስለ ላከው ነው።

- እግዚአብሔር ኢየሱስን መጠበቅ ችሏል?
- አዎን።

- ንጉሥ ሄሮድስ ኢየሱስን መግደል ችሏል?
- አልቻለም።



- ልክ እግዚአብሔር ከረጅም ጊዜ በፊት በነቢያቱ በኩል እንደተናገረው መሰረት እንዲያድነን አዳኙን ላከ።

- ልክ እግዚአብሔር በነቢያቱ በኩል ከረጅም ጊዜ በፊት እንደተናገረው፥ አዳኙ ኢየሱስ በዚህ ዓለም ተወለደ።

- ልክ እግዚአብሔር በነቢያቱ በኩል ከረጅም ጊዜ በፊት እንደተናገረው፥ ኢየሱስ በቤተልሔም ከተማ ተወለደ።

- ኢየሱስ በቤተልሔም ከተማ በተወለደበት ጊዜ ጠቢባን ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ መጥተው ነበር።

ማቴዎስ 2፡1-2

1- በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን፣ ኢየሱስ በቤተልሔም ይሁዳ ከተወለደ በኋላ ጠቢባን ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው፣

2- «የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? በምሥራቅ ኮከቡን አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና» ሲሉ ጠየቁ።

- ጠቢባኑ የሚፈልጉት ማንን ነበር?

- እነርሱ የሚፈልጉት የአይሁድ ንጉሥ ያሉትን ኢየሱስን ነበር።

- ንጉሥ ሄሮድስ ጠቢባኑ የአይሁድን ንጉሥ ለመፈለግ መምጣታቸውን ሲሰማ በጣም ታወከ።

ማቴዎስ 2፡3

3- ንጉሡ ሄሮድስ ይህን በሰማ ጊዜ ታወከ፤ እንዲሁም መላዪቱ ኢየሩሳሌም አብራ ታወከች።

- ንጉሡ ሄሮድስ የታወከው ለምን ነበር?

- ንጉሡ ሄሮድስ ጠቢባኑ ሊፈልጉት በመጡት የአይሁድ ንጉሥ ሥልጣኑን እንዳይወስድበት ፈርቶ ነበር።

- ንጉሡ ሄሮድስ ታውኮ ስለ ነበር የካህናት አለቆችንና የሕግ መምህራንን አስጠራ።

ማቴዎስ 2፥4-6

4- እርሱም የካህናት አለቆችንና የአይሁድ ሃይማኖት መምህራንን በሙሉ ሰብስቦ፥ ክርስቶስ የት እንደሚወለድ ጠየቃቸው።

5- እነርሱም፥ «በይሁዳ ቤተ ልሔም፤ ነቢዩ እንዲህ ብሎ ጽፎአልና አሉ፤

6- «‘በይሁዳ ምድር የምትገኝው አንቺ ቤተ ልሔም፥ ከሌሎቹ የይሁዳ ገዦች በምንም አታንሺም፤ የሕዝቤ የእስራኤል ጠባቂ የሚሆን፥ ከአንቺ ይወጣልና።’»

- ንጉሥ ሄሮድስ የካህናት አለቆችንና የሕግ መምህራንን ምን ጠየቃቸው?

- የአይሁድ ንጉሥ ክርስቶስ የት እንደሚወለድ ጠየቃቸው።

- የካህናት አለቆችና የሕግ መምህራን ምን ብለው መለሱለት?

- እነርሱም ክርስቶስ በቤተ ልሔም እንደሚወለድ ነገሩት።



- አይፈልግም።

- የባሪያ አሳዳሪውም ሆነ ጠንቋዩ ባሮቻቸውን ማቆየት እንደሚፈልጉ ሁሉ ሰይጣንም ሰዎችን ሁሉ ባሮቹ አድርጐ ማቆየት ይፈልጋል።

- ሰይጣን ኢየሱስን ሊገድል የፈለገው በዚህ ምክንያት ነበር።

- ሰይጣን በእርሱ ሥልጣን ሥር ያሉትን ባሮቹን ሊያጣ አይፈልግም።

- ጠቢባኑ ወደ ኢየሩሳሌም ሳይመልሱና ለንጉሥ ሄሮድስ ሳይናገሩ በመቅረታቸው ንጉሥ ሄሮድስ ምን አደረገ?

ማቴዎስ 2፥16-18

16- ሄሮድስ ጠቢባኑ እንዳታለሉት በተረዳ ጊዜ በጣም ተናደደ።
ከጠቢባኑ በተነገረው ጊዜ መሰረት ዕድሜያቸው ሁለት ዓመትና ከዚያም በታች የሆኑትን የቤተ ልሔምንና የአካባቢዋን መንደሮች ወንድ ልጆች ሁሉ ልኮ አስገደለ።

17- በዚህም በነቢዩ በኤርምያስ እንዲህ ተብሎ የተነገረው ተፈጸመ፤

18- «የልቅሶና የታላቅ ዋይታ ድምጽ፥ በራማ ተሰማ፤ ራሔል ስለ ልጆቿ አለቀሰች፤ መጽናናትንም አልቻለችም፤ ልጆቿ ሁሉ አልቀዋልና።»

- ንጉሥ ሄሮድስ በቤተልሔም ከተማ ውስጥና በአቅራቢያዋ የሚኖሩ ዕድሜያቸው ሁለት ዓመትና ከዚያ በታች የሆኑት ወንድ ልጆች በሙሉ እንዲገደሉ አዘዘ።

- ሰይጣን እግዚአብሔር አዳኙን ወደ ዓለም እንደሚልክ አውቋል።

- ንጉሡ ሄሮድስ ኢየሱስን ሊገድለው የፈለገው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ንጉሡ ሄሮድስ ሌላ ንጉሥ ዙፋኑን እንዲነጥቀው ስላልፈለገ ነው።

- ንጉሡ ሄሮድስ ኢየሱስን እንዲገድል ያሳሰበው ማን ነበር?

- ሰይጣን።

- ሰይጣን ኢየሱስን ለመግደል የፈለገው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ሰይጣን ኢየሱስ ሰዎችን ከኃጢአት ኃይል እንዲያድናቸው ስላልፈለገ ነው።

- ምክንያቱም ሰይጣን ኢየሱስ ሰዎችን ከሞት ኃይል እንዲያድናቸው ስላልፈለገ ነው።

- ምክንያቱም ሰይጣን ኢየሱስ ሰዎችን ከሰይጣን ኃይል እንዲያድናቸው ስላልፈልገ ነው።

- አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፡

- አንድ ባሪያ አሳዳሪ ብዙ ባሪያዎች ቢኖሩት ባሮቹን ሌላ ሰው መጥቶ እንዲወስድበት ይፈልጋል?

- አይፈልግም።

- አንድ ጠንቋይ ብዙ ባሮች ቢኖሩት አንድ ሰው መጥቶ ባሮቹን እንዲወስድበት ይፈልጋል?



- የካሕናት አለቆችና የሕግ መምህራን ይህን እንዴት ሊያውቁ ቻሉ?

- የእግዚአብሔርን መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስን ስለሚያነብቡ።

- እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት ከረጅም ጊዜ በፊት በገባው ተስፋ መሰረት ይህ ንጉሥ የሚወለደው በቤተልሔም ነው።

- ከዚያም ንጉሡ ሄሮድስ ጠቢባኑ ወደ ቤተልሔም ሄደው ንጉሡን እንዲፈልጉ ላካቸው።

ማቴዎስ 2፡7-11

7- ከዚያም ሄሮድስ ጠቢባኑን በምስጢር አስጠርቶ በማነጋገር ኮከቡ
የታየበትን ትክክለኛ ጊዜ ተረዳ።

8- ጠቢባኑንም ወደ ቤተ ልሔም ልኮ፣ «ሂዱና ሕፃኑን ፈልጉ፤
እኔም ደግሞ ሄጄ እንድሰግድለት፣ አንዳገኛችሁት ወደ እኔ ተመልሳችሁ የት
እንዳለ ንገሩኝ» አላቸው።

9- ጠቢባኑ ንጉሡ ያለውን ከሰሙ በኋላ ጒዞአቸውን ቀጠሉ። ይህም
በምሥራቅ ያዩት ኮከብ እየመራቸው ሕፃኑ እስካለበት ድረስ ወሰዳቸው።

10- ኮከቡንም ሲያዩ ከመጠን በላይ ተደሰቱ።

11- ወደ ቤትም በገቡ ጊዜ ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩ፤
ተንበርክከውም ሰገዱለት። ሣጥኖቻቸውን ከፍተው ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤም
አቀረቡለት።

- ጠቢባኑ የአይሁድ ንጉሥ ያሉትን ኢየሱስን ባገኙት ጊዜ ምን አደረጉ?

- ሰገዱለት።

- ስጦታዎችንም ሰጡት።

- ጠቢባኑ ለኢየሱስ ስለሰገዱ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ነበር?

- አልተቆጣም።

- ጠቢባኑ ለኢየሱስ ስለ ሰገዱ እግዚአብሔር ያልተቆጣው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

- ኢየሱስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው።

- ከዚያ በኋላ ጠቢባኑ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ለንጉሡ ሄርድስ ነገሩት?

ማቴዎስ 2፡12

12- እግዚአብሔርም ወደ ሄሮድስ እንዳይመለሱ በሕልም ባስጠነቀቃቸው መሰረት፣ መንገድ አሳብረው ወደ አገራቸው ተመለሱ።

- እግዚአብሔር ጠቢባኑ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ለሄሮድስ እንዳይነግሩት በሕልም አስጠነቀቃቸው።

- ስለዚህ ጠቢባኑ በሌላ መንገድ ወደ አገራቸው ተመለሱ።

- ጠቢባኑ ከሄዱ በኋላ እግዚአብሔር መልአኩን ዮሴፍን እንዲያናግር ላከው።



ማቴዎስ 2፡13-15

13- ጠቢባኑ ከሄዱ በኋላ የጌታ መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ተገልጦ፣ «ተነሥ! የምትመለስበትን ጊዜ እስካስታውቅህ ድረስ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ግብፅ በመሸሽ በዚያ ቈይ፤ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይሻልና» አለው።

14- ስለዚህም ዮሴፍ ተነሣ፤ ሕፃኑንና እናቱን ይዞ በሌሊት ወደ ግብፅ ሄደ፤

15- በዚያም ሄሮድስ እስከ ሞተበት ጊዜ ድረስ ኖረ። በዚህም፣ «ልጄን ከግብፅ ምድር ጠራሁት።» በማለት እግዚአብሔር በነቢዩ አንደበት የተናገረው ቃል ተፈጸመ።

- መልአኩ ዮሴፍን በሕልም ምን አለው?

- ማርያምንና ኢየሱስን ይዘህ ሽሽ አለው።

- መልአኩ ንጉሥ ሄሮድስ ኢየሱስን እንዳይገድለው ማርያምንና ኢየሱስን ዮሴፍ ወደየትኛው አገር ይዞ እንዲሂድ ነገረው?

- ወደ ግብፅ።

- ዮሴፍ ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ ማርያምንና ኢየሱስን ይዞ ወደ ግብፅ ሄደ።

- ከረጅም ጊዜያት በፊት ልክ እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት እንደተናገረ፥ ኢየሱስ ወደ ግብፅ ተወሰደ።

- ዮሴፍ ኢየሱስን ወደ ግብፅ ለምን ወሰደው?

- ምክንያቱም ንጉሥ ሄሮድስ ኢየሱስን ሊገድለው ስለ ፈለገ።